# <u>በቅጥፈት  የተሞላ የአቡጊዳዎች ዘገባ</u>

አቡጊዳ የተሰኛው ድህረ ገጽ እጅጉን ከዕውነት የራቀ ዘገባ በድህረገጹ ላይ በማስፈር እውነታው ግን ጨርሶ እንዳይታይ ለመሸፈን እየሞከረ ነው፡፡

በጣም የሚያሳዝነው የወያኔ/ኢህአዴግ አምባ ገነን መንግሥት እንደሚያደርገው ሁሉ የአቡጊዳ ድህረገጽ ባለቤቶችና ተቆጣጣሪዎችም

1ኛ ቅድሚያ ለሃሰት ዘገባ ይሰጣሉ

2ኛ የሜዲያን ዴሞክራሲያዊነት በመዘጋት የሚጥማቸውንና ለነሱ የሚመቻቸውን ብቻ ያወጣሉ በዚህም አባሎቻቸውንም ሕዝቡንም ከዕውነታ የመነጨ ዘገባ እንዳያዳምጥ ማድረግና ጭፍን ድጋፍ ለማግኘት መጣር ነው፡፡

ትላንት ሚያዝያ 20/2002 የሆነውን ሁኔታ አወላክፎ ለማቅረብ የተወሰደው ጥረት ከንቱ አሳሳችና ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ እውነትን መሳት ነው፡፡

በዘገባው ላይ በር ጥሰው ገቡ የሚለው ጨርሶ ያልተደረገና ይልቅስ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ጥቂት ተወካዮች ለኢንጅነር ግዛቸው ጥያቄ ለማቅረብ በስነስርአት ወደግቢው ሲገቡ ኢንጅነር ለማነጋገር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ግቢውን ጥለውና ሚስጥራዊ ትዕዛዝ ለጥበቃው ሰጥተው ወጡ፡፡ ተወካዮቹም ቀድመው ጉዳዩን ከቀናት በፊት ሕጋዊ በሆነው መንገድ  ለፖሊስ አስፈላጊውን ደብዳቤ አስገብተው አሳውቀዋል፡፡ ግን አድሎአዊ የሆነ ተግባር የተፈጸመው በሰላማዊ ሰዎች ላይ ሆኖ ሳለ እንደ አጥፊ ለማቅረብ መሞከሩ አሳፋሪና ከአንድ ለሃገርና ለወገን ቆሜያለሁ ከሚል አካልም የሚጠበቅ አይደለም፡፡

በአቡጊዳ ዘገባ ላይ

.........ይሄን ሁሉ ሲያደርጉ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ከሚቆጣጠረዉ የኢትዮጵያ ቴለቭዥን፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት የሚሰሩት ሥራ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነዉ።

ቢባልም የመርህ ይከበር አባላት ተወካዮች በኢንጅነር ግዛቸው ተጠርተው በመጡት ሰዎቻቸው በዱላ ተቀጥቅጠው ደማቸው እየፈሰሰና የመጠጡበት መኪና መስታወቱ ተሰባብሮ ፖሊስ እያይ እንደገና ተበዳዮቹን አስሮ በዳዮቹን መልቀቁ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ሆነ ፖሊስ ለማን እንዳደላና ከማን ጋር  እንደቆመ በግላጭ የታየ ነው፡፡

‹‹ በአንድነት ስም የተጠራው ስብሰባ ሕገ ወጥ ነው›› ስለተባለውም እንዲህ በርቀት ቅዝምዝም ለመዳኘትና ፍርድ ለመስጠት ከመነሳት በፊት ተንታኝ የተባሉትም ብለው ከሆነ ቀደም ብለው የስብሰባውን ሂደት ለማጣራትና ስህተት ነው አይደለም ለማለት መብቃት ያስፈልጋል፡፡ ስብሰባውን በተመለከተ ሕጋዊና የፓርቲውም ደንብ በሚፈቅደውና በሚያዘው መንገድ ለመከናወኑ ማረጋገጫው ያለ ስለሆነ በተፈለገ ሰአት ለማቅረብ ፍቃደኛ ከመሆናችንም ባሻገር በወቅቱይቻላል፡፡

ማን ስብሰባ እንሚደጠራ ቀንጭቦ ከመጻፍ በፊት ደንቡንና ሕጉን በሚገባ አንብቦ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ደንቡ ምክር ቤቱ ወይም 1/3ኛው የመሥራች ጉባኤ አባላት እያለ ምክር ቤቱ የሚለውን ብቻ ሕዝብን ለማደናገር በታቀደ መልኩ ማቅረብ የሚያሳፍር የልጆች ጨዋታ ነው፡፡

በአቡጊዳና ባለቤቶቹ ስብሰባውን የጠሩት ፕሮፌሰር መስፍን እንደሆኑና ቀደም ሲልም የመርህ ይከበር አስተባባሪ እየተባለ በተሳሳተ ኢንፎረሜሽን ለምን ሕዝብን ለማሳሳት እንደሚሞከር ግልጽ አይደለም፡፡ ፕሮፌሰርም ሆኑ ደበበ ወደዚህ ስብስብ የተጠሩና ለሽምግልና ወደ አመራሩ የተላኩ፤ ግን አመራሩ እምቢተኛ በመሆኑና ወጣቶቹና ሌሎችም አባላት ያነሱት ጭብጥ ካልተስተካከለ ለፓርቲያችን መሪ እስር ደንታ ቢስነትን እያሳየ፤ ይልቁንስ የግል ጥቅምንና ዝናን ያስቀደመ በመሆኑ ከስብስቡ ጋር አብረው ለመታገል ተቀላቀሉ፡፡ ይህስ ግላዊ የሆነው ውሳኔያቸውና የፓርቲያቸውን መሪ እስራት ከቸልታ አመለካከት ለማውጣት የቆሙለት ዓላማ እንዴት በክፋት ይተረጎማል፡፡ ይህ እንግዲህ ግለሰቦች የፈጠሩት የሃሰት መንገድ ነውና ወደ እውነቱ መመለስ ነው የሚያዋጣው፡፡

የሚያዝያ 20ውን ውሎ በተመለከተ ዕውነታው የሚከተለው ነው

***ሚያዝያ*** 20/2002

## እነ ኢንጅነር ግዛቸው አዲስ የተመረጡትን 11 የአንድነት አመራር አስደብድበው አሳሰሩ።

አዲስ የተመረጠው አመራር በመስራች ምክር ቤት አባላት ውሳኔ መሰረት አስቀድሞ የዕቃና ንብረት ርክክቡን በተመለከተ ደብዳቤ ለኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው ለማድረስ ከትናንት በስቲያ ማክሰኛ ዕለት ወደ ጽ/ቤቱ አዲስ የተመረጡት አባላት ቢሄዱም ኢንጅነር ግዛቸው ደብዳቤውን አልቀበልም በማለት እምቢታቸውን ከመግለጻቸውም ባሻገር ጽ/ቤቱም እንዳይቀበል አዘዙ።

የሄዱት ተመራጭ አባላትም  የእምቢታው ውሳኔ አግባብነት የሌለው ቢሆንም በማክበር ከግቢው ለመውጣት መንገድ ሲጀምሩ ዘለፋና ዛቻ በማሰማት ትንኮሳ ቢኮረኩሩም ተወካዮቹ ግን ሰላማዊና ስነ ስርአታዊ በሆነ ታጋሽነት ከግቢ ወጥተዋል። ምንም እንኳን ኢንጅነር አልቀበልም ቢሉና አቶ አስራትና፣ አቶ አንዱ ዓለም፣ አቶ ንጉሴ(የድርጅቱ ጠበቃ) አቶ ብሩ በርመጂና ምክትል ጸሃፊው አቶ መስፍን፣ እመውጫው ድረስ እየተከተሉ በማንጓጠጥና በስድብ ነገር ለመቀስቀስ ቢጥሩም ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ይህም በተወካይ አዲስ ተመራጮች ያውም ወጣቶች፣ ጠብ ቢጀምሩ አንድም ሰው ላይተርፍ እንደሚችል ቢያውቁም የአንድነትን ስም ለመጠበቅና በእስር ያለችውን መሪ ክብር ላለማጉደፍ በማሰብ ተሰድበውና ተዘልፈው መውጣትን መርጠዋል።

ዛሬም እንደገና በፖስታ የተላከው የአደራ ደብዳቤ መድረሱን ካረጋገጡ በኋላ ለርክክቡ ወደ ግቢው ሲገቡ ኢንጅነር ግዛቸው ከግቢው በመውጣትና ለጥበቃውም አንድም ሰራተኛ እንዳይገባ መመርያ በመስጠት ከአካባቢው ተሰወሩ።ጉዳዩ ያልገባቸው የአዲሱ አመራር ተመራጮች ወኪሎች፣ ኢንጅነር ሲመለሱ ካልተመለሱም ደብዳቤው የደረሰ በመሆኑ ከጽ/ቤቱ ቀጠሮ ለመቀበል ግቢው ውስጥ ገብተው በመጠበቅ ላይ እንዳሉ በድንገት በሩ ተከፍቶ አባላት ያልሆኑ ጎረምሶች ወደግቢው ገቡ፣ተከትለውም ኢንጅር ግዛቸውና አጋሮቻቸው በመኪና ሆነው በመግባት ኢንጅነር ግዛቸው ይዘዋቸው የመጡትን ጎረምሶች በሰላማዊ መንገድ ሲጠብቋቸው ወደ ነበሩት ተወካዮች እያመለከቱ ‹‹በሏቸው›› የሚል ትዕዛዝ ስለ ሰጡ ተዘጋጅቶ የተቀመጠውን አጣና እያወጡ በቅድሚያ አቶ ለሜሳ የተባሉትን የቀድሞም የመስራች ምክር ቤት አባል የአሁኑም ተመራጭ ግንባራቸውን ፈነከቱ፣ወኪሎቹ የሄዱበትን መኪና የፊት ለፊት መስታወት ሰባበሩ ከዚያ በኋላ ወጣቶቹን አንድም ነገር በጃቸው የሌለውን በአንድነት መርህ መሰረት ሰላማዊ ሆነው የሄዱትን በጫካና የአውሬ ሕግ የኢንጅነር ሎሌዎች የያዙት አጣና እስኪሰባበር አወረዱባቸው።

እጅጉን የሚገርመው ግን ወኪሎቹ አንዳችም ስንዘራ አለማድረጋቸውና እየተደበደቡ መቆማቸውና በተደጋጋሚ ‹‹ሠላማዊ ትግል እያልን እንዴት ዱላ ታነሳላችሁ ደሞስ ዱላን ምን አመጣው›› ቢሉም ሰሚ ሳያገኙ እንደእባብ ተቀጥቅጠው አቶ ለሜሳም ደማቸውን እያፈሰሱ ወደ ሆስፒታል ሄዱ።

እንግዲህ ሃገርና ሕዝብ እናስተዳድራለን ብሎ ምሎ የተገዘተ አመራር በሰላማዊ መንገድ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ በአዲሱ መድረክ አመራሮች ደንብና፣ መድረክ ከሕወሃት መንደር ካመጣው በለው ቀጥቅጠው መመርያ ለዚህ መብቃት የነኢንጅነር ግዛቸውን ዝቅጠትና የአመራር ብቃት ማነስ ነው የሚያሳየው።

እጅጉን የሚገርመው ደግሞ ያ ቢሮ የአንድነት ሆኖ ሳለ፣ ኪራይም የሚከፈለው ለአንድነት ተብሎ ምንም ቢያንስ  ከሃገር ውስጥም ከአባላት በሚሰበሰብና አብላጫው ደግሞ ከዲያያስፖራው በሚገኝ መዋጮ ሲሆን ቢሮዎቹ ላይ በሙሉ ‹‹የአንድነት›››››››› የሚለው ተነስቶ ‹‹የመድረክ .......››በሚል ተለውጦ መታየቱ አንድነት ምን ያህል እየጠፋና በመድረክ እየተዋጠ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል።

እነ ኢንጅነር ግዛቸው ወደ ዱላ የገቡበት ዋነኛ ምክንያት በየትም አካባቢ በከተሞችም በክልሎች ተቀባይነት በማጣታቸውና ቢሮዎች ሁሉ ‹‹ልቀቁ አዲስ አመራር ተመርጧል አስረክቡ የሚለው ግፊት ስለበዛባቸው በጀብደኝነትና በምስለኔ አገዛዝ ተስፋ ለማስቆረጥ የተደረገ ሙከራ ነው፡፡በስተመጨረሻው ገደማ በነኢንጅነር‹‹ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል››ዓይነት ደምወዝ እየተከፈላቸው የሚሰሩት የፓርቲ አባላት ድርጅቱ ስርአት የያዘ እንደሆነ አሁን የምናገኘው ጥቅማ ጥቅም ይቀርብናል በሚል ስጋት ኡኡታ በማሰማታቸው ፖሊስ በመምጣቱ የተደባደቡት ጉልበተኛ ቅጥር ዱለኞች ግቢውን ለቀው ለመሰወር ሲሞክሩ ተደብዳቢዎቹ እንዳይወጡ አድርገው ፖሊስ በጉዳዩ ቢዘገይም ገብቶ የተጎዱትን ወደ ሆስፒታል ልኮ የተሰበረውንም መኪና በማስረጃነት መዝግቦና ቃል ተቀብሎ ሂደቱን በማጣራት ላይ ሳለ ንጉሴ ነውጤ የተባለው የአንድነት የልምድ ተቀጣሪ ጠበቃ ከሳሽ ሆኖ ተብዳቢዎችላይ ክስ መሰረተ፡፡ ለፖሶቹም የንጉሴን ክስ ተቀብለው በአካባቢ የነበሩትን ምስክሮች ቃል ተቀብለዋል፡፡ ምስክሮቹ በሙሉ እነ እንጅነር ደብዳቢዎች መሆናቸውን መስክረውባቸዋል፡፡ያም ሆኖ ግን እነስዬና ነጋሶ፣ገብሩ አስራትና አንዱዓለም እንዲሁም ሌሎች በስተመጨረሻው የጉዳዩ ባለቤት በመሆን ለፖሊስ አዛዦች በሰጡት ሃሳብ መሰረት ተደብዳቢ የሆኑትና ንብረታቸው የተሰባበረባቸው፣ 11 በመስራች የጉባኤ አባላት የተመረጡት አመራር ወኪሎች ታስረው እንዲያድሩና ደብዳቢዎቹና የህወሀት ወገንተኛ የሆኑት ወገኖች ደብድበውም ንብረት ሰብረውም በነጻ እንዲሄዱ ተደርጎ የአንድነት የመርህ ተሟጋቾችና በጠቅላላ ጉበኤው የተመረጡት ታስረው እንዲያድሩ ተደርጓል፡፡

እንግዲህ ቀደም ሲል ዝም አንልምች በመንግሥት ይደገፋሉ እየተባሉ በሰሜን አሜሪካ የአንድነት የድጋፍ አሰባሳቢ አመራሮች ሲወነጀሉ የነበረው ለእስር ተዳረጉ፡፡የመድረክ አመራሮችና ደጋፊዎች ግን ወንጀል ሰርተው ፈንክተው ሰብረው በነጻ ወደቤታቸው በክብር ተሸኙ፡፡

ግርማ ካሣ የሚባለው የመድረክ በሰሜን አሜሪካ ሳይመረጥ በወዶ ገብነት የመድረክ አገልይና የአቶ አክሎግ አፈ ጉባኤ አንዳንድ የመርህ ይከበር አመራሮች የወያኔ/ኢህአዴግ አገልጋዮች ናቸው እያሉ ሲወነጅሉና መሰሎቻቸውምም ሲያናፍሱት የነበረው የሃሰት አሉባልታ ዕውነቱ አግጥጦ ወጣ!!

ማን ሆነ የወያኔ/ ኢህአዴግ ሎሌ ታዲያ!!!

11ንዱ የአመራር ተመራጮች በቅድሚያ በኡራኤል ፖሊስ ጣቢያ የተበዳይ ቃላቸውን እንዲሰጡ ሆኖ ወደ አመሻሹ ላይ ወደ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ተወስደው ከማታው በ3 ሰአት ገደማ ደግሞ አዳራቸው ቁራ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ሆኖ ወደዚያው ተወስደው አዳራቻው እዚያ እንዲሆን ተወስኖ ገብተዋል፡፡